# ጨዋታ ፈረሰ—ዳቦ ተቆረሰ

ከድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ

ሙዙን ብርቱካኑን
        ግሮሰሪ ሄደና
የተባዮች ፊሊት
        ከሱቅ ጨመረና
የአይጥ መርዙንም
        ከመንገድ ገዛና
ቆሎውን በሶውን
        ለጠፍ አረገና
ቤተሰብ ወዳጁን
        ደህና ዋሉ አለና
ሊጎበኝ ጓዶቹን
        ቃሊቲ ሊያቀና

የፎርዊል መኪና
        ድምፁ ስለሳበው
ቀና ብሎ ባይኑ
        በደንብ ተከተለው
የፌኩን ቅንጅት
        ምክትሉን አየው
ሰላምታን አቅርቦ
        ገብቶ ተዳበለው

ሃሳቡን ሲነግረው
        ሳይፈፅም ጨርሶ
ዘራፍ አለ ጌታው
        አየለ ጫሚሶ
ፈቃድ ማን ሰጥቶህ ነው
        ዘለፈው መልሶ
ተመስገን ዘውዴንም
        ቀንደኛውን ጠቅሶ
የወንጀሉን ብዛት
        አክብዶ አባብሶ
ምስጢር አመራሩን
        መንግሥትንም ጠቅሶ
ወቀሳ ዘለፋ
        ወንጀልም ታድሶ
ሳይደብቅ ጠቆመው
        መሆኑን ምሰሶ
ባለብዙ ጌቶች
        የማይወድቅ በስብሶ

በባዕድ በመንግሥት
        ዕውቅናን ተላብሶ
በትዕቢት በንቀት
        መሪዎቹን አንኳሶ

የቃሊቲ እሥረኞች
        ወህኒ የወረዱት
ይቅርታ ጠይቀው
        ዕውቅና ካልሰጡት
ውድ ፓርቲያችንን
        በወጉ ካልሾሙት
አዲሱን ትብብር
        ባስቸኳይ ካልሻሩት
ከአፍራሽ ዳያስፖራ
        ካላስቆሙ ትችት
ለኢትዮጵያችን ሰላም
        ይቆዩ ወህኒ ቤት
ፍትህ ዲሞክራሲ
        ይታደግ በሂደት
በመንግሥት አመራር
        እንሥራ ባንድነት
ምስጋናም ይገባል
        ለሰጠንም ሕይወት
ዋስትናም ተችሯል
        ቢመጣብን ምፃት
በል ስማኝ ወዳጄ
        ይቅርብህ ጉብኝት
እንዲያ ወረድ ብለን
        እንጎንጭ ድራፍት
ቃል የማን ዕዳ ነው
        በጊዜህ ተደሰት

የአመራሩ ሂደት
        ግራ ስለገባው
የአሠራሩ ነገር
        መላ ስለጠፋው
የጨበጣው ሤራ
        ብልጭታ ሲታየው
ምስኪኑ ጠየቀ
        ናላውን አዞረው

ወገኔ ታስሮብኝ
መጠየቅ ካልቻልኩኝ
የትግል ጓዶቼን
አይዞአችሁ ካላልኩኝ
ቢያሻኝ ከቃሊቲ
ፓርላማ ካልሄድኩኝ
ድንቄም ዲሞክራሲ
መተንፍስ ናፈቅሁኝ

አይቼሽ አይቼሽ
ተመልክቼሻለሁ
አዲሷ አረማሞ
ቻዎ ብዬሻለሁ
ይቅርታ ወገኖች
እኔ በድያለሁ
ሱባኤ ልገባ
እርዳታ እሻለሁ
ምህረት እንዳገኝ
ፀሎት ጀምሬአለሁ

ስለቴን ለማግባት
ቃሊቲ እመጣለሁ
ታቦቱ ሲወጣ
አብሬ እነግሣለሁ

ጨዋታ ፈረሰ
ዳቦ ተቆረሰ
የቁጩው ቅንጅት
በቃ ፈራረሰ
ድሮስ ድቡሽት ላይ
መቺ ቤት ተቀለሰ
የመሠሪው ውጥን
ተፈረካከሰ
የእንግዴ ልጅ ሤራ
ከሽፈ ረከሰ
ቅንጅት መንፈሱ
በሕዝብ የነገሰ
ማዕበሉ መቼ
ሱናሚ ደረሰ

*************************

© ድሚልኝ ብህሬ - ዘአዲሱ ገበያ
ሐምሌ 1998
zeaddisu_gebeya@yahoo.com
July 2006